# „አለባብሰው ቢያርሱ ባአረም ይመለሱ“

ያለን፣ የሆነን፣ የተደረገንና በመደረግ ላይ ያለን ነገር እንደሌለ ለማደረግና ለመሸፋፈን መሞከር ባንድ ወገን፣ የሌለ ነገር ፈጥሮ „ጠብ ያለሽ በዳቦ“ ማለት በሌላው ወገን፣ ሁለቱም የቧላ ቧላ የሚያደርሱት ጉዳት ያንደኛው ከሌላኛው የሚተናነስ አይሆንም። የቀደመው ያመረቅዝና ሲፈነዳ መድሃኒቱን ማግኘት ችግር ሲሆን፣ የቧለኛው ደግሞ „ተቀምጠው የሰቀሉት ቆሞ ለማውረድ ይገዳል“ እንዲሉ ላርምህ ቢሉት ማጣፊያው ያጥርና ሊደርስ የማይገባ ጥፋት ይደርሳል።

በቀደመው ሃሳብ ላይ ልቆይና የባቢሎን ሰዎች በ72 ቋንቋ ተናገሩ ሲባል እኛ ወደ 80 ከፍ አድርገን 80 የተለያየ ቋንቋ የሚናገሩ ጎሳዎች/ነገዶች/ብሔሮች/ ብሔረሰቦቸ አሉን። የቋንቋው መብዛት በመሰረቱ ብዙ አይደለም። ከኛ የበለጠ 150-200 ያሳደጉ ብዙዎች ስላሉ። አንባቢዎች ከመጠሪያ ስሞቹ የሚጥማችሁን መርጣችሁ የመያዝ  መብታችሁን አከብራለሁ። እኔ ነገድ የሚለው ቀልቤን ስለሳበው፣ እሱን ይዤለሁ። ይሁንምና፣ እነዚህን የሕብረተሰብ ክፍሎች አጼዎቹም፣ ወታደሩም፣ የትግሬ ሕዝብ ነጻነት ግንባርም አልፈጠሯቸውም። ድሮም ነበሩ፣ አሉ፣ ይኖራሉም። በዚህ ሃቅ ላይ ጠብ  አይኖርም የሚል እምነት አለኝ። የሚያነጋግረን ጉዳይ ግን፣ ነገዶች የችግር ምንጭ መሆናቸውን የሚመለከተው ነው። የችግር ምንጭ ስል ሲፈጠሩ ለችግር ፈጠራ ተብለው ተፈጠሩ ማለቴ እንዳልሆነ ግን ግልጽ ይሁን። ለማለት የፈለግሁት ዛሬ በኢትዮጵያ እንደሚ ታየው ነገድን ማዕከል ባደረገ የሚጧጧፈውን ትርምስ፣ የርስ በርስ መጋጨጥና ሌላም ሌላም ቸግርን ለማመላከት ነው።

በርግጥም ሲፈጠሩ ለችግር የተፈጠሩ አይደሉም የሚለው እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የነገዶቹ የማንነትም ሆነ ሌላ ጥያቄ ፈጽሞ የሚነሳበት ምክንያትም ሆነ ሌላ  አጋጣሚ አይ ኖርም፣ ሊኖርም አይችልም ብሎ ለመደምደም የሚያስችል ምንም ዓይነት መተማመኛ ሊኖር ባይችልም፣ ጥያቄው ዛሬ በሃገራችን ወደደረሰበት ደረጃ እንዳይደርስ ተደረጎ ቀደም ያለ መፍትሄ ሊያገኝ ይችል እንደነበር ይታየኛል። „ካያያዝ ይቀደዳል ካነጋገር ይፈረዳል“ እንዲሉ፣ የነገዶች ጥያቄ ማቀምቀም የጀመረው በዚህ ቀን፣ በዚሕ ሰዓት፣ በዚህ ዓመት፣ በዚህ ቦታ ብሎ መጥቀስ ባይቻልም፣ ቢያንስ ከ50ዎቹ ዓመታት ወዲህ ነው ብንልና በአጼ ሃይለሥላሴ የአገዛዝ ዘመን ጥያቄው እንዴት እንደተስተናገደ እንደ ምሳሌ ላንሳውና፣

በኢትዮጵያ ውስጥ የብዙሃን ፓርቲ ስርዓት መመስረት ያስፈልጋል፣ ፖለቲካ ፓሪቲዎች እንዲቋቋሙ መፈቀድ አለበት፣ የሚል ሃሳብ ለንጉሡ በአንዳንድ የቅርብ ሰዎቻቸው ሲቀርብላቸው፣ ሃሳቡን ላለመቀበል ዋና መከላከያ አድርገው የሚሰጡት ምክንያት „አሁን ይህንን ብንፈቅድ ሁሉም በየነገዱ ልደራጅ ይልና አገር ይበታተናል“ የሚል ነበር ይባላል። በዚህም ምክንያት የብዙሃን ፓረቲው ሥርዓትም እንዳይመሰረት፣ የነገዶቹ ጉዳይም መፍትሄ ከሚፈለግለት ይልቅ ታፍኖ እንዲቆይ ተደረገ። በርግጥ ንጉሱ ለብዙሃን ፓረቲው ስርዓት ስስ ልብ ኖሯቸው እንዳሉትም በነገድ ተደራጅቼ መበታተንን ላምጣ ይላል የሚለው ዕውነትነት አለው ቢባል እንኳን፣ በዙ ሀገሮች እንደመፍትሄ የተጠቀሙበትና ዛሬም የሚጠቀሙበት ዘዴ ነገድን ወይም ሃይማኖትን መሰረት ያደረገ የፖለቲካ ሥልጣን ለመያዝ የሚደራጅ የፖለቲካ ፓርቲ በሕገ-መንግሥት እንዲገደብ በማድረግ ችግሩን ዛሬ ከደረሰበት ደረጃ እንዳይደርስ ማድረግ ይቻል ነበር። ጉዳዩ እነደዛሬው የተለያየ አቅጣጫ ይዞ ባልጠዘበት ጊዜ በዚህ መልክ መፍታት አይቻልም ነበር ቢባል ውሃ የሚቋጥር ክርከር አይሆንም።  ይህ ሲባል ግን ከዚያው ጋር ሳይነጣጠል መደረግ ያለበትም፣ ነገዶቹ ባህላቸውንና ቋንቋቸውን ለማሳደግና ለመንከባከብ የሚኖራቸው መብት መከበር ብቻ ሳይሆን፣ መንግስትም እራሱ ጉደዩ አድረጎ የሚተጋበትም መስከ መሆኑ ጭምር ይሰመርበታል። የንጉሡ መከላከል ምክንያት ለውጡ ስልጣናቸውን ጥያቄ ውስጥ ስለሚያስገባ ብቻ እንደነበር ብሎ መገመቱ ወደ ዕውነቱ ያስጠጋናል።

ያም ሆነ ይህ፣ ታፍኖ የተያዘው የነገዶቹ ጉዳይ ኖረ ኖረና የትገሬ ሕዝብ ነጻነት ግንባር የሚባል አገር አጥፊ እጅ ወደቀ። ይሄ ድርጅት በዓለም ላይ ምሳሌ የማይገኝለት፣ በኢትዮጵያ ብቻ የታየ ክስተት የሆነውን፣ የማዕከላዊ መንግሥትን ጨብጦ እገዛዋለሁ የሚለውን ሕዝብ በየነገዱ እንዲደራጅ በማስገደድ፣ ጠንካራ ሕብረ-ብሄር ድርጅት እንዳይኖር በማድረግ፣ አልፎ ተርፎም ነገዶችን በፈለጋቸው ጊዜ ጥለው መሄድ የሚያስችላቸው ሕገ-መንግሥት በመቅረጽ፣ አንዱን ነገድ ከሌላው ጋር በማጋጨት፣ እዚያው በዚያው መልሶ አስታራቂ መስሎ በመቅረብ፣ ዛሬ ያንዱ ወዳጅ ሌላ ጊዜ የሌላው በመሆን፣ የሥልጣኑ ማቆያ አድረጎ እየተጠቀመበት ያለ ዘረኛ ሃይል ነው። በዚህም ምክንያት ያልተረጋጋች ኢትዮጵያን ፈጥሮ፣ ዛሬ ዜጎቿን አገራቸው መቼና እንዴት ትበታተን ይሆን እያሉ ወደሚቆዝሙበት ደረጃ ላይ ያደረሰ መሆኑን፣ ረጋ ባለ መንፈስ ለሚታዘብ ሁሉ ወለል ብሎ የሚታይ ሃቅ ነው። ይህ በምሳሌ የቀረበ ሃሳብ የታፈነ ሃቅ/ችግር ሲፈነዳና ያልታሰበ እጅ ሲወድቅ ስለሚያስከትለው ጦስ በቂ ማሰረጃ እንደሆነ በማመን ወደዋና ጉዳዬ ልሻገር፣

ሰሞኑን ቢያንስ የዲያስፖራውን ሚዲያ በማጣበብ ላይ የሚገኝ በኢትዮጵያ ውስጥ እየተደረገ ያለ የሕዝብ መፈናቀል ዜና አለ። አዎ! መፈናቀል ነበር፣ አለ፣ ይኖራልም ለኢተዮጵያ ብቻ ተብሎ ከሰማይ የወረደ ጉዳይ አይደለም። በዚህም ስምምነት አይገደንም። ሕዝብ በተለያዩ ምክንያቶች ይፈናቀላል፣ በጦርነት ምክንያት፣ በሌሎች የተፈጥሮ አደጋዎች እንደጎርፍ፣ ቃጠሎ፣ ረሃብ፣ ቸነፈር ሁሉ የመፈናቀል ምክንያቶች ሊሆኑ ይችላሉ፣ ከዚያም በተጨማሪ፣ ሊሆን የማይገባው ግን የሚሆንና እየሆነም ያለ የመፈናቀል ምክንያትም አለ። ይህም በጎዶሎ አስተዳደር በተለይም የገዥዎች እንጂ የተገዥዎች ድምጽ በማይሰማበት ሥርዓት ምክንያት የሚፈጸም መፈናቀል ነው።

በሀገራችን እየተደረገ ስላለው መፈናቀል ይህቺን ማስታወሻ እንድጽፍ ያነሳሳኝ ዋና ምክ ንያት፣ በአንዳንድ የድርጅትና እንዲሁም ነጻ ሚዲያ ድህረገጾች ላይ ጉዳዩን አስመ ልክተው በሚያወጡዋቸው መግለጫዎች ላይ ያስተዋልኩት አቀራረብ ነው። መግለ ጫወቹ በቤኒሻንጉልና በጉራፈርዳ የተደረጉትንና በመደረግ ላይ ያሉትን መፈናቀሎች በጋምቤላ፣ ባፋር፣ በራያ፣ አዲስ አባባ፣ ድሬ ዳዋ፣ መቀሌ ከተደረጉት መፈናቀሎች ጋር ዓንድ ዓይነት አድርገው ለማቅረብ ይሞክራሉ፣ ከፍ ብዬ እንዳልኩት፣ መፈናቀሎች ሁሉ የተለያዩ ምክንያቶች እንዳሏቸው ጠቁሚአለሁ።

ብሎም በጉራፈርዳና በቤኒሻንጉል የተፈጸሙት መፈናቀሎች ምክንያት በጋምቤላ፣ ባፋር፣ ራያ፣ አዲስ አባባ፣ ድሬ ዳዋ፣ መቀሌ ከተደረጉ መፈናቀሎች ምክንየት የተለየ ነው። እላይ ከዘረዘርኳቸውም የተለያዩ ምክንያቶች ካንደኛቸውም ጋርም አይቀራረብም።

የጉራፈርዳና የቤኒሻንጉል ተፈናቃዮዎቹ እንዳሉትና ሌሎችም ማስረጃዎች እንደሚመሰ ክሩት የሚሉት፣ አማራ ስለሆናችሁ እዚህ መኖር አትችሉም ወደክልላችሁ ሂዱ ተብለን ተባረርን ነው። በዚህ መልክ የተፈጸመ ማፈናቀል በሌሎቹ የተለያዩ አካባቢዎችና ከተሞች የተደረጉ መፈናቀሎች በአንዳቸውም አልታየምም አልተሰ ማምም።

ታዲያ እነዚህን ሁለት ዓይነት መፈናቀሎች አድበስብሶ ለማቅረብ መሞከር፣ በጽሁፌ መግቢያ ለማሳየት እንደሞከርኩት የሚታይንና ያለን ችግር በሌሎች አነስተኛ ችግሮች ጥላ ስር ሸፋፍኖና አፍኖ በመያዝ፣ በጊዜው አስፈላጊውን መረባረብ በማድረግ መፍትሄ እንዳያገኝ ተደርጎ ለትውልድ የሚተላለፍ ችግር በይደር ከመያዝ ያለፈ ፋይዳ አይኖ ረውም። ውጤቱም ከላይ በንጉሡ ጊዜ በነገዶች ጥያቄ የተፈጸመውን ጥፋት ዓይነት መድገም ነው የሚሆነው።

ይህንን ችግር ጊዜ ወስዶ፣ መንፈስን አረጋግቶ፣ ልብ ብሎ ማየቱ ጥሩ ነው። አንድን ነገድ ከዚህኛው ሰው የተለየ ቋንቋ ስለምትናገር ሌላው በዋለበት አትውልም ብሎ ወደ ክልልህ ሂድ ማለት እኮ! ልክ ደቡብ አፍሪካ በአፓርታይድ ዘመን ይፈጸም የነበረውን ዓይነት አፈጻጸም ማለት ነው። ልዩነቱ ደቡብ አፍረካ በነጭና በጥቁር መካከል የተደረገ ሲሆን፣ አገራችን ውስጥ እየተፈጸመ ያለው አንዱ ከሌላው የተለየ ቋንቋ ተናጋሪ በመሆኑ ነው።

በጋምቤላ፤ ባፋር፤ በራያ፤ አዲስ አባባ፤ ድሬ ዳዋ፤ መቀሌ ወዘተ የተደረጉ መፈናቀሎች ይህንን ቋንቋ ስለተናገርክ ከዚህ ክልል ለቀህ ውጣ የተባለ የለም፡፡ በነዚያ አካባቢዎች የተደረገውን የሕዝብ ከቦታው ማስነሳትን መፈናቀል ያሰኘው ምክንያት ሊሆን የሚች ለው፤ መንግሥት ለሥራ ይፈልገዋል፤ ወይም መንገድ፤ ድልድይ ወዘተ ይሰራል በሚል ምክንያት ሆኖ፤ ይህ ደግሞ በየትኛውም ጊዜና ቦታ፤ በየትኛውም አገር የሚፈጸምና ሲፈጸምም የኖረ፤ ወደፊትም ሊፈጸም የሚችል አሰራር ስለሆነ፤ አግባብነቱ ጥያቄ ውስጥ የማይገባ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ነገር ግን ከስፍራቸው እንዲነሱ የሚደረጉት ሰዎች አስፈላጊው ካሳና ምትክ ቦታ ሳይሰጣቸው፤ የመኖሪያ ቤታቸውንና ቤትና ንብረት አጥፍቶ መጠጊያ በማሳጣት ለችግር የዳረገ ሲሆን፤ የዚህ ዓይነት ሰብአዊ መብት ጥሰት በመፈጸሙ ሊሆን ይችላል። እንዲህ ከሆነም በዚሁ መልክ ሊወገዝ ይገባዋል። የአማ ራው ጉዳይ ግን፤ ካሳ ከመክፈልም ሆነ፤ ምትክ ቦታ ከመስጠት ጋር የሚያገናኘው አንዳችም ነገር የለም። የጉራፍረዳውና የቤኒሻንጉሉ መፈናቀል በዘረኝነት ላይ የተመ ሰረተና በመጠረፍ (ዲፖርት በመደረግ ነው) መፈናቀሉ የተፈጸመው። ስለሆነም መስተናገድ ያለበት ከዚህ ጠባዩ አንጻር ነው።

ከዚህም ተነስተን በድፍረት፤- በትግሬ ሕዝብ ነጻነት ግንባር አገዛዝ ባማራው ሕዝብ ላይ የዘር ማጽዳት ወንጀል ተፈጽሟል፤ እየተፈጸምም ነው። በማጽዳቱ ስራ ምክንያት ባማራው ሕዝብ ላይ የደረሰ በቀላሉ የማይሽር ጠባሳ አለ፤ ይህ ጠባሳ ከዘር ወደዘር እንዳይተላለፍ በዚሁ ትውልድ እንዲያበቃ መደረግ አለበት፤ ተመሳሳዩ እንዳይፈጸምም ቃል ይገባ፤ እያልን ኢትዮጵያውያን ሁሉ ባንድ ላይ እንጩህ! መፍትሄው ተራራ አይሰወጣም፤ ቁልቁለት አያስወርድም፤ በጅ፤ በደጅ ያለ ነው።

የመፍትሄው መጀመሪያ፤ በጋዛ ሃገሩ ከየሚኖርበት አካባቢ የዘር ማጽዳት ዘመቻ ሰለባ የሆነውን የአማራ ሕዝብ የትግሬ ሕዝብ ነጻነት ግንባር መንግሥት ከልብ የመነጨ፤ ቁስልን የሚያሽር ይቅርታ መጠየቅ፤ የተባረረ በሙሉ ነገ ዛሬ ሳይባል ወደቦታው እንዲመለስ ማድረግ፤ ለተባራሪው ቅድስት አገር ያቺ ነችና! ለጠፋበት ነብረት ብቻ አይደለም፤ የሞራል ካሳም መክፈል፤ ይህን ለመፈጸም ሰው መሆንንና እንደሰው ማሰብን ብቻ ነው የሚጠይቀው። የተፈጸመውን ጥፋት በምኑም በምኑም አለባብሶ መተዉ፤ „አለባብሶ ቢያርሱ ባአረም ይመለሱ" እንደተባለው፤ ምናልባት ለጊዜው እነዲያንቀላፋ ማድረግ ይቻል እንደሆን እንጂ፤ አይተኛም ብለን ሁላችንም ባንድ ቃል ለመናገር ትንፋሽ አይጠረን። ባጭሩ እንዲቀጭ ማድረግ አለብን። የዚህ አይነት ጥፋት ሁለተኛ ባገራችን እንዳይሰማ የሁን። የበሽታው ታፍኖ መቅረት ከጉዳት በስተቀር፤ ለማንም፤ ለምንም የድንቡሎ ያህል አይጠቅምም።

እዚህ ላይ ተጨማሪ ልብ ማለት ያለብንና ልዩ አጽንኦትም ልንሰጠው የሚገባ አጋጣሚ ያለ ይመስለኛል። ይህም በደቡብ አፍሪካ ለተፈጸመው አሰቃቂ የአፓርታይድ ሥርዓት መገልገያ ሆኖ የቆየ „ክልል" የሚባለው ቃል ነው። እሱም ባስቸኳይ ከሃገራችን ምድር ላይ መወገድ የሚገባው በሽታ ነው። በርግጥ የክልልን አግባብ የለሽነት ገና በተፈ ጠረበት ጊዜ ጀምሮ ተቃውሞ አልተደረገበትም ለማለት ሳይሆን፤ አሁን ሁኔታው የበለጠ አንገብጋቢ ያደርገዋል ለማለት ነው። ኢትዮጵያወያን በሰሜን፤ በደቡብ፤ በምስራቅ በምዕራብ ከጎረቤት አገሮቻችን የሚለየን ድንበር አለን። እሱ በቂያችን ነው። ክልል ለከብቶቻችን፤ የሳር መጋጫ ቦታ መለያ ይሁን። ሰላማዊ ጊዜ እመኛለሁ።

አገራችንን ካነጃበበባት አደጋ ሁሉ አምላክ የጠብቃት

ቶላ ጋሞ
tollagamo@ymail.com